## ስህተቶች፤

1. የውድድሩ ፕሮግራም ለማንኛውም ቡድን በጽሁፍ አልተሰጠም።
2. መስራች የሆነው የባሮ ቡድን ለስብሰባ አልተጠራም። ነገር ግን ውድድሩን ያልተካፈሉና ለብዙ አመት ለመካፈል ፈቃደኛ ያልነበሩ ቡድኖች ለስብሰባ ተጋብዘዋል።
3. የደረጃ ጨዋታ በሎተሪ መሆኑና መሰረዙ ተመልካችን ሊያጉላላ በቅቶአል። ከዚህም ሌላ የዋንጫ ጨዋታውን ሰአት አዛብቶአል።
4. ባለፈው ስድስት አመታት ባደረግነው ውድድር በተለያዩ ምክንያቶች ቡድኖች ወደ ሜዳ ዘግይተው ሲመጡ አስተያየት ተደርጎ በመጡበት ሰአት ጨዋታው ተካሄዶአል።በቫንኩቨር በተደረገው ውድድር የባሮ ቡድን ዘገየ ተብሎ በፎርፌ ጨዋታው ቆመ። በህጉ መሰረት የፎርፌ ውሳኔ ጨዋታው ከመጀመሩ በፊት ለባሮ ቡድን አልተነገረውም። ነገር ግን ጨዋታው በባሮ አሸናፊነት ካለቀ በሁዋላ በሚስጥር ለተሸናፊው ቡድን ዋንጫ በመስጠት የባሮን ቡድን ስሜት ለመንካት ሙከራ ተደርጉዋል።

ስለዚህ ወደፊት የሚደረጉትን ውድድሮች የባሮ ቡድን ለመካፈል የሚከተሉት መስፈርቶች መምዋላት አለባቸው።

1. በህዝብ ፊት ያላግባብ የተወሰደብን ዋንጫ እንዲመለስ፤
2. የመተዳደሪያ ደንብ እንዲዘጋጅ፤
3. የአመራርና የአዘጋጅ ኮሚቴ እንዲመሰረት፤
4. የዚህ ውድድር መስራች

በዚህ አመት የሚደረገውን ውድድር አስመልክቶ ግን የባሮ ቡድን የዚህ ውድድር መስራችና አባል የነበረውን የፖርትላንድ ቡድን መሪ የአቶ ሽመልስ ገሰሰን መታሰቢያ እንዲሆንና ውድድሩ በፖርትላንድ ከተማ እንዲደረግ ስለተጠየቅን ወደ ካልጋሪ መጥተን ውድድሩን መካፈል አንችልም።

ለዚህ ውድድር ማደግና መጠናከር የሁልጊዜ ምኞታችን ነው።

ዮሃንስ ወልደ ማሪያም

ፕሬዝደንት
ባሮ ስፖርትስ ክለብ

## ግልባጭ

ፖርትላንድ አቢሲኒያ ክለብ
ፖርትላንድ የኢትዮጵያ ክለብ
ሲአትል ክለብ
ቫንኩቨር ክለብ
ዊኔፔግ ክለብ
ኤድመንተን ክለብ
ቪክቶሪያ ክለብ

Created by trial version, http://www.8848soft.com